

ከልብ የሆነ ፍቅራችንና  ጥልቅ የሆነ ሐዘናችንን እንገልጻለን::
ሙሉጌታን የሚያውቀው ሁሉ “ወዳጇ” እያለ ዘወትር ከሰላምታው  በፊት
የሚ ቀበልበትን መልካም አንደበት ምንጊዜም አንረሳም::

ከመድሐኔዓለም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን

# አቶ ሙሉጌታ ገብሬ

ታህሳስ 25, 1952 - ጥቅምት 23, 2011




# Mulugetta Gabre

**December  1952–  October 2011**



# የአቶ ሙሉጌታ ገብሬ አጭር የህይወት ታሪክ



አቶ ሙሉጌታ ገብሬ ከእናቱ ከወ/ሮ ዘለቀች ሣዱራ እና ከአባቱ አቶ ገብሬ ጫሶ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ታህሳስ 25 ቀን 1952 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ። ወላጆቹ በንግድ ሥራ የሚተዳደሩ ስለነበሩ፤ የበኩር ልጃቸው የሆነውን ህጻን ሙሉጌታ ገብሬን ይዘው ወደ ሐረር ከተማ ሄዱ።

ሙሉጌታ ገብሬ ለትምህርት እንደደረሰ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ሐረር ከተማ በሚገኘው የመንፈሳዊ ትምህርት ቤት፤ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በልዑል ራስ መኮንን ትምህርት ቤት፤ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በሐረር መድሃሐኒዓለም ትምህርት ቤት አጠናቀቀ።

የሁለተኛ ደረጃ የመልቀቂያ ፈተናውን በጥሩ ውጤት ከአለፈ በኋላ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ጥንት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሚባለው) በመግባት ትምህርቱን በመከታተል ላይ እንዳለ፤ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ1970 በተነሳው የተማሪዎች ንቅናቄ ዩንቨርሲቲው ስለተዘጋ በኢትዮጵያ አየር መንገድ የአውሮጵላን ጥገና ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት(Aircraft Maintenance Technician schooll) በመግባት የሁለት ዓመት ስልጠና አጠናቆ በዲፕሎማ ተመረቀ።

በ1972 ዓ.ም. የአውሮፕላን ሞተር ጥገና ክፍል በመደልደል ሥራውን ጀመረ። ዩኒቨርስቲውን እንዲለቅ ያደረገው የትግል እንቅስቃሴ ብልጭ እና ድርግም ሲል ቆይቶ በ1974 ዓ.ም. ስለፈነዳ ትግሉን መቀላቀል ግድ የሚለው ሆነ። በዚህ የትግል ወቅት የወጣት ማህበሩን ( Youth Legue) እና የሠራተኛውን ማህበር በማቀናጀት ለተወሰነ ጊዜ እንደሠራ ሥልጣን በጨበጠው ወታደራዊ መንግስት ሥለተጋለጠ በከተማው ውስጥ የሚካሄደውን የሕቡዕ እንቅስቃሴ ለመቀጠል ተገደደ።

በከተማው ሕቡዕ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳለ ወታደራዊው መንግስት የሱን እና መሰሎቹን ፎቶግራፍ በከተማ ውስጥ በማሰራጨት አሰሳ በመጀመሩ ከተማውን ለቆ ወደ ትግራይ ክፍለ ሐገር በማቅናት በአጋሜ አውራጃ ሠንገዴ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ የኢሕአፓን ሠራዊት ኢሕአሠን ተቀላቀለ።

በትግራይ ክፍለሐገር የአጋሜን አውራጃ ጨምሮ በአድዋ፤ በክለተአውላሎ እና ጎንደር ክፍለሐገር በመዘዋወር በተለያዩ አውራጃዎች ሲታገል ቆይቷል።

ሙሉጌታ ለዲሞክራሲ፤ ለእኩልነት በጠቅላላው ለሰው ልጆች መብትና ልዕልና ረሃብና ጥማቱ ሳይበግረው የኢትዮጵያውይንን መብት ከነጠቀው ወታደራዊ

## ሙሉዬ

ታመህ ሳትተኛ ወዳጅ ሳይጠይቅህ
ለማንም ሳትነግር ለቤተዘመድህ
በምሽት ተነስተህ ወዴት ትሄዳለህ?
ረጭ ባለው ሌሊት በጨረቃው ድምቀት
ዘኒ ናት ወይ መጥታ ፍቅሬ ና! ያለችህ
ወይንስ በሌ ነወይ? በፉጨት የጠራህ
ሄኖክዬ ነውይ? ኳሱን የሊጋልህ
እኮ! ተናገር ሙሉዬ አፈር ስሆንልህ
ያደረክልኝን እንዴት ብዬ ልርሳው
ብቆጥር ብሰፍር ማለቂያ የሌለው
መጠለያ እንዲሆን ከዛፉ ገንጥለህ ከሣሩም በጥሰህ
ከድንጋይ ፈልፍለህ ከጎጆው ቀልሰህ
ሲበርደን ደርበህ ሲሞቀን አውልቀህ
ሲጠማን አጠጥተህ ሲርበን አጉርሰህ
ያደረክልኝን እንዴት ብዬ ልርሳው
ብቆጥር ብሰፍር ማለቂያ የሌለው
የፍቅርህ ነፀብራቅ ከትከሻህ ደምቆ
ይሄው ይታየኛል ደመናን ሰንጥቆ
ያ! ወርቃማው ድምፅህ በቀጭኑ ሺቦ ሠላምታ ጠፍሮ
በፍቅር በአክብሮት ከች ሲል ከጆሮ
እንዴት ብዬ ልርሣው? ተቸገርኩ ዘንድሮ
የአብዬ ገብሬ ልጅ የፍቅር ሙያህ የሚያበራ
እስትንፋስህ ፀጥ ብሎ ሥራህም ቆሞ የሚያወራ
ጉልበትህም ላመ ምነው ክንድህ ዛለ
የስትንፋስህ ፀዳል ፀጥ ብሎ ዋለ
እስቲ ስምህን ላንሳ ስቅ ይልህ እንደሁ ድንገት
ያገር አድባር ወርካው የኮሚኒቲው ንብረት
የአብዬ ገብሬ ልጅ የአራት ልጆች አባት

*ከቆንጆት ፈቃደ እና*

*ያሬድ ልሣነወርቅ*

መንግሥት መንጋጋ ፈልቅቆ ለማውጣት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ለሦስት ዓመት ሲታገል ቆይቶ ሁኔታው ላሰበው ዓላማ ፍጻሜ ላይ የማያደርሰው መሆኑን ስለተረዳ የሚወዳትን እናት ሀገሩን ኢትዮጵያን ለቆ ወደሱዳን መሰደድ ግድ ሆነበት፡፡

ሙሉጌታ ሱዳን በነበረበት ጊዜ ከሁመራ እና ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለሐገር በጨቋኙ የደርግ መንግሥት በግድ ከየገባያው እየታፈሱ ወደጦር ግንባር ከተወሰዱ በኋላ አምልጠው ወደሱዳን የተሰደዱትን ወታደሮች በማሰባሰብ ሜዳ ከቀረው የኢሕአሠ ሠራዊት ጋር በማገናኘት በጽናት ትግሉን ቀጠለ።

በ1979 ዓ.ም. በሚታገልበት በኢሕአፓ/ ኢሕአሠ ድርጅት ውስጥ በተነሳው አለመግባባት ትግሉን ለመቀጠል አስቸጋሪ ሆኖ ስላገኘው፤ ሲታገል እና ሲያስትግል የነበረውን ድርጅት ለቆ ዳግማዊ ሰደቱን ሱዳን በገባ ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ በግንቦት ወር 1981 ዓ. ም. ወደ ሰሜን አሜሪካ ሲያትል ዋሺንግቶን አቀና።

ሲአትል ዋሽንግተን (Seattle, Washinton) እንደገባ አንድም በሙያው በአየር መንገድ ተቀጥሮ መሥራት ወይም ያቋረጠውን ትምህርት መቀጠል በሚለው ሃስብ ለብዙ ጊዜ ከራሱ ጋር ከታገለ በኋላ ሚዛኑ ወደደፋበት ትምህርት በ1982 ዓ.ም. ሲአትል ኮሚኒቲ ኮሌጅ (Seattle Community College) በመግባት ትምህርቱን ቀጠለ።

የሁለት ዓመቱን የኮሚኒቲ ኮሌጅ ትምህርቱን አጠናቅቆ በዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ (University Of Washintonon) በመግባት በኤሌትሪካል ኢንጂነሪንግ (Elctrical Engineering) የመጀመሪያ ዲግሪውን በ1986 ዓ.ም. አጠናቀቀ። ዳግም ፑልማን (Pullman) በሚገኘው ዋሽንግተን እስቴት ዩኒቨርስቲ (Wshington State Univr-sity) በመግባት ሁለተኛውን ዲግሪውን እየሠራ ሳለ Renton የሚገኘው Kenworth ተብሎ የሚጠራው የTrack ኩባንያ ለሥራ ስለጠራው ስራውን ተቅብሎ በInstrument design ለአንድ ዓመት ያህል ሲሠራ ቆየ።

በዚህ ሥራው ላይ እንዳለ በሙያው እና በተማረበት ከዚህም ቀደም በኢትዮጵያ አየር መንገድ ይሠራበት ከነበርው የአውሮፕላን ጥገና ጋር የተያያዘ ሥራ በማግኘቱ Kenworthን ለቆ Evrett, Washington በሚገኘው የቦይንግ ኩባንያ በ1991 ሕይወቱ እስካለፈበት ጊዜ ድረስ በኤሌክትሪካል ዲዛይን(Electrical Design) በቦይንግ 767፣ 777 እና 787 ለሃያ ዓመታት ሲሠራ ቆይቷል።

በ1989 ዓ.ም. ውድ የትዳር ጓደኛ የሆነችውን ወይዘሮ ዘነበች አደራን በማግባት ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለየችው ድረስ አራት ልጆች አፍርተው አብረው በፍቅር ኖሩ። ባለቤቱ ወይዘሮ ዘነበች አደራ በሞት ከተለየችው ዕለት ጀምሮ የናታቸውን ሞት እንዳያስቡ አራት ልጆቹን አራት ዓመት ሙሉ በትዕግስት እና በጥሩ እንክብካቤ

ብቻውን ያለ እናት ሲያሳድግ ቆይቶ በተውለደ በ 58 ዓመቱ ጥቅምት 23 ቀን 2011 ዓ.ም. በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ተለየን።

አቶ ሙሉጌታ በነበረው ልዩ ተወዳጅ ባሕሪዎች በሲያትልና ኣካባቢው በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እጅግ የተከበረና አንደ ሕብረተሰብ ዓምድ ለመታየት የበቃ ነው፡፡ ህሙማንን በመጠየቅ፡ ያዘኑትን በማፅናናት፡ ይተጎዱትን በማበረታታት ለብዙዎቻችን ችግር ፈጥኖ ደራሽ ስለነበረ ትዝታው የማይረሳ ነው፡፡ ያጋጠሙትን ፈተናዎች በሙሉ በተዕግሥትና በበጎ መንፈስ በመመልከት ሊወጣቸው ችሏል፡፡

ሙሉጌታ ከአንደበቱ ክፉ ቃል የማይወጣው ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን የተላበስ በመሆኑ ትዕግሥቱ ለብዙዎቻችን አርአያ ሆኗል፡፡

በመጨረሻም በአቶ ሙሉጌታ ገብሬ ድንገተኛ ዕረፍት በቤተሰቡ ላይ ለደረሰብን ከባድ ሀዘን ለማፅናናት አብራችሁን ለሰነበታችሁትና እንዲሁም በገንዘብና በምክር ለረዳችሁን ሁሉ ከልብ የሆነ ምስጋናችንን እያቀረብን ብድራችሁን ለመመለስ ያበቃን ዘንድ አምላካችንን እንለምናለን፡፡

ልጆቹ፡- ሉሊት ፤ ሜሪ ፤ ኢያሱና ዮሴፍ ሙሉጌታ
እህቱ፡ የሺ ገብሬ
ወንድሞቹ፡- አማረ ፤ ሰለሞን ፤ አዳነ ፤ ተስፋዬ ፤ መኮንንና መኩሪያ ገብሬ

Mulugetta's special life sadly ended on October 23rd, 2011 suddenly, abruptly, and at the age of 58.
**Rest in Peace Mulu!**

Last but not least, to all of you that are gathered together all through these very dark and difficult days, we want to thank you from the bottom of our heart for being here sharing our darkest and most difficult days. We appreciate your time, we admire your support, we are grateful for your financial contributions and your comforting words.

God Bless all of you! We give our gratitude for having you in our lives during these days when we are in deep sorrow beyond words. Please take care of each other! As you can see, life can sometimes be very short not to care about one another.

Live Fully, Love Openly, and go make a difference like Mulugetta and Zenebech did!

Thank you,

From His Children…. Lulit , Merry, Eyassu and Yossef Mulugetta
His Sister… Yeshi Gabre
His Brothers … Amare, Solomon, Adane, Tesfaye, Mekonnen and Mekuria Gabre

lives together. They were like Abraham and Sara.

Out of their true love they were blessed with four wonderful children that now are survivors of both Mulugetta and Zenebech (their mom who died four years ago).

Both Mulugetta and Zenebech were role models to their communities, their friends and colleagues…they are known, respected, loved, and now remembered for their kind words, heartfelt smiles, for their patience, for their endurance in time of trials and tribulations.

It is as if they are one and the same when they visit those who are ill, when they comfort those who are heartbroken, when they give courage to those who mourn the loss of loved once.

They are the first to arrive and offer help when help was needed. These two couples are made for heaven, even God don't seem to want to keep them apart.

Mulgetta did his best to be an exceptional father that he was. He even tried to cover the missing part, as he tried to be both dad and mom. He dedicated himself to his children. He raised them alone for the last four years. He tried to look for good things in life even on his difficult days.

Mulugetta lived his life as a gentleman! He never raised his voice with rage. He was a true Ethiopian in how he treated all people with respect and kindness. We all are blessed to have known a man of such character.

Then, the stress of being a perfectionist in all things he ever did, and living without his soul mate, and raising teenagers by himself was too much to take. He was only human!

# Mr. Mulugetta Gabre's Brief Life Story

Mr. Mulugetta Gabre was born in the city of Addis Ababa Ethiopia, on December 25$^{th}$ 1952 European Calendar, from his mother Mrs. Zelekech Sadura and his father Gabre Chaso.
Because his parents were merchants' they moved from Addis Ababa to Harer, Eastern Ethiopia and they took their first born child Mulugetta with them.

As Mulugetta became a school age boy, he was enrolled in missionary school where he attended all of his elementary schooling. Then, he was transferred to Lul Rass Mekonen Middle School. He then attended all of his high school years at Harer Medhanealem high school.

After completing his high school years with excellent GPA (Grade Point Average), he was enrolled in Addis Ababa University which used to be known as Kedamawi Haileselassie University.
But, his enrollment was short-lived as it was interrupted by constant riots that the University Students lead in 1970s; which at the end caused the University to totally shutdown.

At this stage, Mulugetta decided to take a different route. He was enrolled in Ethiopian Airlines Aircraft Maintenance Technical School. After two years of training, he graduated with Diploma.

In 1972 European Calendar, he started working for Ethiopian Airlines in the department of Airplane Engine Maintenance.

Meanwhile, the struggle and the riots by the University Students continued although on and off. In 1974, the revolution happened and Mulugetta felt strongly to be part of the revolution and he played a role in coordinating the Labor Associations and the youth League. But, soon he end up being one of the wanted men who were hunted by the new Military Junta.

The Military Junta posted his picture as one of the most wanted!

That is when Mulugetta left the city of Addis Ababa and headed north to the province Tigray to join the freedom fighters against the military Junta.

After three years of participation in the armed struggle against the regime, he was forced to flee to the Sudan and work on a new mission. While in Sudan, he was re-grouping his units also attracting deserters from the army to join the resistance force. His honesty, determination and high regard for his county men earned him a great trust among his compatriots. He was instrumental in convincing many soldiers to change sides during his stay in the Sudan.

In 1979, after continuously fighting for years to guarantee Ethiopian People the Freedom they deserve, a new conflict within his own party forced Mulugetta to change course and migrate to the United States in May of 1981.

As he settled in Seattle Washington, he thought about working as an Airplane Technician or goes back to school and earn a degree. After contemplating with those ideas for some time, he then decided to go back to school.

In 1982 he was enrolled in Seattle Community College and earned his Associate Degree. Mulugetta immediately transferred to University of Washington where he studied Electrical Engineering and received his Bachelor Degree in 1986.

As Mulugetta went back to school to get his second degree and was attending at Washington State University in Pullman, he was offered a Position with a company in Renton Washington named Kenworth Track Company. He accepted the offer and came back to work for them as Instrument Designer and worked for about a year.

In 1991 he took a new position with Boeing in Everett Washington. Since his new position includes using the knowledge he accumulated from going to Ethiopian Airline Maintenance Technical School, and let him use his years of experience that he gained working for Ethiopian Airlines, plus apply what he had learned as Electrical Engineer, it felt right to be working for Boeing.

Mulugetta worked for Boeing as an Electrical Designer from 1991 to the day that he took his last breath. He had worked on Boeing 767,777and 787.

Mulugetta’s personal discipline weren’t only on his educational follow through, his political stand and commitment, his work ethics but he was true to his word dedicated loving husband and an amazing dad to his four children.

In 1989, he was married to his lovely wife Zenebech Adera and they had a life that can truly be defined as a real Christian Marriage! They lived with out fault no matter how big of an adversity they had to face in their